# ሕዝብና ቤት ቆጠራ
# ኮሚሽን ጽ/ቤት

# ዜና ቆጠራ ካርታ



ከቆጠራ ካርታ ዓላማዎች አንዱ፡

**ባቆጠራ ወቅት የቁጥጥር ተግባርን ለማቀናጀት የመስክ ሥራ ክንውንን በተገቢው መንገድ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ነው።**

ቅፅ 01 ቁጥር 002 ነሀሴ 1996

አድራሻ
ስልክ 578100
ኢ.-ሜይል popcen@telecom.net.et
ፋክስ ቁጥር 251-1-56-38-85
ፖ.ሣ.ቁጥር 59047

ማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት

## የሕቤቆኮ ጽ/ቤት ራዕይ( vision)

የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ራዕይ " የሕዝቡን ኑሮ

ለማሻሻል መሠረት የሚሆን ሕዝብና

ቤትን የተመለከተ ወቅታዊና አስተማማኝ

መረጃ ያላት ኢትዮጵያን ተፈጥራ ማየት"

ነው!!

# መልእክት

አገራችንን ዛሬ ከምትገኝበት የድህነት አረንቋ ለማውጣትና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን ለማምጣት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ፣ ፕላኖችን ለመንደፍም ሆነ በሥራ ላይ የዋሉትን ፕሮግራሞች ውጤታማነት ለመገምገም አስተማማኝና ወቅታዊ የሥነ-ሕዝብ መረጃ መኖር የግድ አስፈላጊ ነው። ከዚህም በላይ ለመልካም አስተዳደር መስፈንና ለዲሞክራሲ ማበብ የሥነ-ሕዝብ መረጃ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነው። በየአስተዳደር እርከኑ የሚካሄዱትሕዝባዊ ምርጫዎች በትክክለኛ የሕዝብ መረጃ አሰፋፈር፣ የአድሜ ክልል ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ትክክለኛና አስተማማኝ መረጃ መሰብሰብ ይኖርበታል።

በአጠቃላይ የሕዝብ መረጃ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ዕቅዶች ለሠላምና ለመልካም አስተዳደር፣ ለዲሞክራሲ ስርዓትም ሆነ ለተረጋጋ ስርዓት መስፈን የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። «መረጃ ታላቅ ሃብት ነው» የሚባለውም በዚህ ምክንያት ነው። ይሁን እንጂ መረጃ ሃብት የሚሆነው ትክክለኛ አስተማማኝ እና ወቅታዊ ሲሆን ብቻ ነው። እንደሚታወቀው አንድ መረጃ ትክክለኛና አስተማማኝ ነው የሚባለው በትክክለኛው መንገድ የተሰበሰበ ሲሆንና በመሬት ያለውን ገጽታ ሲያንጸባርቅ መሆኑ ግልጽ ነው። መረጃ ሲሰበሰብ በጥንቃቄና የዜግነትን ሃላፊነት ግምት ውስጥ ባስቀመጠ መልኩ ካልሆነ ውጤቱ አስከፊ፣ ቀውሱም በሀገርና በህብረተሰቡ እድገት ላይ ጎጂ አስተዋጽኦ ያለው ነው።

ከዚህ አንፃር የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ሠራተኞችም ሆኑ ባጠቃላይ የካርታ ሠራተኞችና ተቆጣጣሪዎች በመንግሥትና በሕዝብ የተጣለባቸውን ኃላፊነትና አደራ ችሎታቸው በፈቀደው መጠን እየተወጡ መጭውን የህዝብና ቤት ቆጠራ ዕቅድ ለስኬት ማብቃት ይጠበቅባቸዋል።

ከሁሉም በፊት እነዚህ ሠራተኞች በጋራ መገንዘብ ያለባቸው አቢይ ነገር ቢኖር የቆጠራ ቦታ ካርታ በትክክል ካልተሠራ የዋናውን ቆጠራ ውጤት የተዛባ እንደሚያደርገውና በየትኛውም መስክ የሚዘረጉትን የልማት ውጥኖች በማደናቀፍ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ማህበራዊ እድገት ኋላቀርነት ዋነኛው ምክንያት ሲሆን መቻሉን ነው።እርግጥ፣የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ የአንድ መንግሥታዊ አካል ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ይልቁንም የተደራጀና የተቀናጀ የሕዝብ ድጋፍና የየአስተዳደር እርከኖችን ያልተቋረጠ እገዛ በእጅጉ የሚጠይቅ ነው። የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የሚሰበስበው መረጃ የሚጠቅመው የሁሉንም ዜጎች ህይወት ለማሻሻል የሚደረገውን የልማት እንቅስቃሴ ሁላችንም ልንረባረብ ይገባናል።

ስለዚህ በቢሮም ሆነ በመስክ ላይ ያላችሁ የጽ/ቤቱ ሠራተኞች እንደሁልጊዜው በትጋትና በጥንካሬ የሙያ ግዴታችሁ እንድትወጡ አደራ እላለሁ።

አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የሥራና የብልፅግና እንዲሆን

በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ስም ከልብ እመኛለሁ።

አማረ ኢሳይያስ

ዋና ፀሐፊ

# <u>የአዘጋጇ መልእክት</u>

ሥራ ህይወት ነው፣ በመሥራት የሕዝብን ኑሮ ማሻሻልና ሀገርን መገንባት ይቻላል፣ በሥራ አማካኝነት አድገት፣ ብልጽግናና ልማት ይጨበጣል፤ ሥራ ወዳድ የሆነ ሕዝብ ርሃብን፣ ድህነትንና ኋላቀርነትን በተባበረ ክንድ እየዳሰ ወደልማትና ብልጽግና ይሸጋገራል። በዓለም ላይ እጅግ የበለፀጉ ሀገሮች ታሪክ እንደሚያስገነዝበው ሀገሮችና ህዝቦቻቸው እዚህ ከመድረሳቸው በፊት ሌትና ቀን ያለመታከት ሠርተዋል። ዕድሜና ፃታን ሳይለይ ለህይወታቸው መሻሻል ያለዕረፍት አምርተዋል። ከሳብና ድካማቸው ፍሬም እነሆ ከነሱ አልፈው ለሌሎች ህዝቦች መድህን እስከመሆን ደርሰዋል። ይህ እንግዲህ የጥረትና የልፋታቸው ውጤት ነው።

እኛ ኢትዮጵያውንም ስንፍናን በመርታትና የሥራ ባህላችንን በማሳደግ ጠንክረን ከሠራን ካደጉ ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ የሚፈጅብን ጊዜ ያጥራል። እርግጥ ነው ሁሉም ነገር የሚገበየው በጊዜ ነውና በጊዜ ሠርተን ለመጠቀም ሁላችንም ራሳችንን ካዘጋጀን ሀገራችን የምትጠብቅብንን በማበርከት የጎላ አስተዋፃ ልናደርግ እንበቃለን። ይህ ከሆነ ደግሞ ለነገ ልጆቻችን የተሻለ ህይወት አዘጋጀንላቸው ማለት ነው። ዛሬ እያንዳንዳችን በአሮጌው ዓመት መገባደጃና በአዲሱ ዓመት መባቻ ላይ ሆነን ያሳለፍናቸውን ድፍን 12 ወራት ወደኋላ በመቃኘት ከትናንት የተሻለ ዛሬንና ነገን ለመሥራት ታጥቀን መነሳት ይኖርብናል።

በዚህ መንፈስ ሆነን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ጽ/ቤት የመስክ ሠራተኞችንና መላውን ሕዝብ አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የጤናና የሥራ እንዲሆን ምኞታችንን እንገልፃለን።

<u>ዜና ቆጠራ ካርታ</u> መጽሔት በሁለተኛ እትሟ የካርታ ሠራተኞችን መጣጥፎች ጨምሮ የጽ/ቤቱን ገጽታ የሚያሳዩ፣ በቢሮና በመስክ እየተከናወኑ ያሉትን ዋና ዋና ተግባራት ታመላክታለች። ዜና መጽሔቷ የሁላችንም በመሆኗ በአብሮነት አብረን እንድንዘልቅ አንባቢዎቿን ሁሉ «እጃችሁ ከምን?» ትላለች። በመጨረሻም <u>ማግለልና አድልዎን</u> አስወግደን በመተሳሰብ እንድንኖር ዳግም ጥሪዋን ታስተላልፋለች። የከርሞ ሰው ይበለን!

**መልካም አዲስ ዓመት!**

ውድአላት ገዳሙ

ነሐሴ 1996

# ዜናዎች

## አፈ- ጉባዔው የሥራ መመሪያ ሰጡ

የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ክቡር አቶ ዳዊት ዮሐንስ ሐምሌ 29/96 ዓ.ም በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የቀረበላቸውን ሪፖርት በማድመጥ የሥራ መመሪያ ሰጥተዋል።

አፈ-ጉባኤው ከሪፖርቱ በተጨማሪ በመስክ የተሠሩ የቆጠራ ቦታ ካርታዎች እንዴት በዲጂታይዝ ሲስተም ወደ ኮምፒዩተር ቋሚ መረጃነት እንደሚለወጡ በባለሙያዎች የተደረገውን ገለፃ ከተመለከቱ በኋላ በ1999 ዓ.ም ለሚካሄደው ሦስተኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ስኬት በአሁኑ ወቅት ጽ/ቤቱ እያካሄደ ያለውን የቆጠራ ቦታ ካርታ ዝግጅትን በማበረታታት የጽ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሆነው ኮሚሽን በቅርብ ከጽ/ቤቱ ጋር በመገናኘት ሥራውን እንዲከታተል አመራር ሰጥተዋል። ክቡር አቶ ዳዊት ዮሐንስ በተጨማሪም ጽ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት እየሰራ ያለው የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራም ሆነ ቀጣዩ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ግዙፍ ተግባራት ለሀገሪቱ ጠቃሚ መረጃ የሚሰጡ ታላላቅ ክንዋኔዎች በመሆናቸው ሥራውን በተሳካ መልኩ ለመቋጨት እንዲቻል ጽ/ቤቱ ከሌሎች አጋር መ/ቤቶች ጋር በመደጋገፍ መሥራት እንደሚጠበቅበት አሳስበዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት በተካሄደው በዚህ ስብሰባ ላይ የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላትና የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

## የኮሚሽኑ ፪ኛ መደበኛ ስብሰባ ተካሄደ

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ፪ኛ መደበኛ ስብሰባ ነሐሴ 17/96 ባደረገው ዓመታዊ የአባላት ስብሰባ በኮሚሽኑ ጽ/ቤት የተከናወኑትን የ1996 የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በመገምገምና የ1997ን የበጀት ዓመት ዕቅድ በማጽደቅ ተጠናቀቀ። በብሔራዊ ሆቴል ለግማሽ ቀን በተካሔደው በዚሁ ስብሰባ የጽ/ቤቱ ዋና ጸሐፊ አቶ አማረ ኢሳይያስ የጽ/ቤቱን የእንቅስቃሴ ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት እንደተገለፀው

ጽ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት በአብይነት እየተንቀሳቀሰ ያለው በ1999 ዓ.ም ለሚካሄደው ለ3ኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ተግባር በሆነው በቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ላይ መሆኑ ተብራርቷል።

ክቡር ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈጉባኤና የኮሚሽኑ አባል በመሩት በዚህ ስብሰባ ላይ የክልል መንግሥታት ርእሰ መስተዳድሮችና ም/ርእሰ መስተዳድሮች የተገኙ ሲሆን የኮሚሽኑን ዓላማና የእለት ከእለት ተግባር ለማስፈፀም የተቋቋመው ጽ/ቤት ባከናወናቸው ተግባራትና ባጋጠሙት ችግሮች ዙሪያ ሰፊ ውይይት በማድረግ ለችግሮቹ የመፍትሔ እርምጃዎችን ቀይሷል።

ከዚህም ባላይ ኮሚሽኑ በ1999 ዓ/ም ለሚካሄደው የ3ኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ስኬት በቀዳሚነት እየተከናወነ ያለው የቆጠራ ቦታ ካርታ ዝግጅት በስፋትና በጥራት እንዲቀጥል ለጽ/ቤቱ አመራር ሰጥቷል።

ጽ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት 45 የካርታ ቡድኖችን አደራጅቶ በማሠማራት በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት የቆጠራ ቦታ ካርታ እየሠራ ሲሆን እስካሁን ከነሐሴ 10/95 እስከ ሰኔ 30/96 ድረስ ባለው ጊዜ 17,926 የቆጠራ ቦታ ካርታዎችን አዘጋጅቷል። ይህ አፈፃፀም በበጀት ዓመቱ ከተያዘው ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር 20.7% ብልጫ ያለው ቢሆንም በመጭዎቹ የሁለት ዓመት ተከል ጊዜአት ውስጥ በሀገሪቱ በጠቅላላ ይሠራል ተብሎ ከታቀደው 90,000 (ዘጠና ሺህ) የቆጠራ ቦታ ካርታ አንፃር ሲታይ ገና 1/5ኛው ብቻ ነው። ቀሪውን ሥራ ለማጠናቀቅ እንዲቻልም አስፈላጊ የሆኑት የመሥሪያ ቁሳቁሶች ተሟልተው ለጽ/ቤቱ መቅረብ እንደሚገባቸው ስብሰባው አጽንኦት በመስጠት በተለይ ጽ/ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል ያጋጠመውን የተሽከርካሪ እጥረትና የቢሮ ጥበት ቅድሚያ ወስዶ መፍትሔ ለመስጠት የሚችል አካል ሰይሟል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 103 መሠረት በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 180/91 የተቋቋመ መንግሥታዊ አካል ሲሆን ዓላማውም፣

1ኛ/ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮችና ለምርጫዎች ዕቅድ

*ዝግጅት፣ ለዕቅድ አፈፃፀም፣ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ለምርምር የሚጠቅሙ ሕዝብና ቤትን የሚመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ማጠናቀር፣ መገምገም ብሎም ማሰራጨት.*

2ኛ/ *የሕዝብና የቤቶች ምዝገባ በመላ ሐገሪቱ እንዲቋቋምና እንዲሰራበት መሠረታዊ ጥናቶችን በማካሄድ የሚደራጁበትን መንገድ መቀየስ ናቸው።*

አንድ የቆጠራ ቦታ ካርታ ማለት 150 - 200 ቤቶችን በከተማና እንዲሁም ከ150 - 200 ቤተሰቦችን በገጠር የያዘ የቀበሌ ክልል ማለት ሲሆን ጠቀሜታውም አንድ ሰውና አንድ ቤት ሳይቆጠር እንዳይቀርና ድጋሚ እንዳይቆጠር ሆኖ በተጨማሪ በአንድ አካባቢ ያለውን የመሠረተ ልማት አገልግሎት ሁኔታ፣ የሕዝብ አሠፋፈርና ስለሌሎችም ጉዳዮች በቂ መረጃ በመስጠት የናሙና ጥናቶችን ለማካሔድ የሚረዳ ፍሬም ለማዘጋጀት የሚያገለግል ነው።

የኮሚሽኑ የ1996 ዓም በጀት ዓመት እንቅስቃሴ አበረታች መሆኑ ተገለፀ

የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ግንቦት 11/96 ዓ.ም በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ለበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበው የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈፃፀም ዘገባ ጽ/ቤቱ ከፍተኛ ጥረት የታከለበት እንቅስቃሴ ማድረጉን የሚያመላክት እንደሆነ ተገለፀ ። ይህ የተገለፀው የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የበላይ አካል በሆነውና በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በበጀትና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ አባላት ሲሆን ኮሚቴው የተጠቀሰውን ዓመት ሪፖርት ካዳመጠ በኋላ እጅግ ውስን በሆነ በጀት ጽ/ቤቱ የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራን በማከናወን ያስመዘገበው ውጤት አበረታች መሆኑን ገልጾ፣ የሕዝብ ብዛትን ማወቅ ሐገሪቱ እያካሄደችው ላለው የድህነት ቅነሳ ፖሊሲ ጉልህ ሚና እንደሚጫወት አስገንዝቧል።

## የጽ/ቤቱ የስትራቴጂክ እቅድ ሰነድ ተዘጋጀ

የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት( ከ1997-1999) ላለው ጊዜ የሚመራበትን ስትራቴጂክ ዕቅድ ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑ ተገለፀ። ይህ የተገለፀው ሐምሌ 20/96 በነበረው አጠቃላይ የሠራተኞች ስብሰባ ላይ ሲሆን በሀገሪቱ እየተካሄደ ያለው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም አንዱ አካል የሆነውና የኮሚሽኑን ጽ/ቤት ራዕይ፣ ተልዕኮ የሥልጣን ምንጮችና ዓላማ ማዕከል በማድረግ የተዘጋጀውን ይህን ዕቅድ ተፈፃሚ ለማድረግ ሁሉም ሠራተኛ በፅናት እንደሚታገል በዚሁስብሰባ ላይ የጋራ አቋም ወስዷል።

ካለፈው የበጀት ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ በአቢይና በንዑሳን ኮሚቴዎች አማካኝነት ከፍተኛ ዝግጅት ሲደረግበት የቆየውን ይህን ስልታዊ ዕቅድ በታለመለት ጊዜ ውስጥ እውን ለማድረግ ይቻል ዘንድ የእያንዳንዱን ሠራተኛ የነቃ ተሳትፎ እንደሚጠይቅ የጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ አማረ ኢሳይያስ በመዝጊያ ሥነሥርዓቱ አሳስበዋል።

## ትምህርትና ስልጠና

ሐገሪቱ እየተከተለችው ባለው የአቅም ግንባታ ፖሊሲ መሠረት ጽ/ቤቱን በሰለጠነ የሰው ኃይል ለማደራጀት እንዲቻል የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ባለሙያዎቹን በሐገር ውስጥና በውጭ ሀገር በማስተርስ ዲግሪ መርሐ-ግብር በማስተማር ላይ መገኘቱ ከጽ/ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

በዚሁ መሠረት ሁለት ባለሙያዎች በደቡብ አፍሪካ እየሰለጠኑ ሲሆን በሐገር ውስጥም አራት ባለሙያዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች እየተማሩ ሲሆን ከነዚሁ ሰልጣኞች መካከል አንዷ ሴት መሆኗንም ለማወቅ ተችሏል።

ከዚህም በላይ በአጠናቀቅነው የበጀት ዓመት ሁለት የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በስታስቲክስ በማስተሬት ዲግሪ ተመርቀዋል።

# የኢትዮጵያ የአካባቢ መረጃ መረብ

/ETHIOPIAN ENVIRONMENTAL INFORMATION NETWORK/

በኃይሉ ገ/መድህን

ሕ.ቤ.ቆ.ኮ ጽ/ቤት

የአፍሪካ አካባቢያዊ ሁኔታ/Environmental Situation/ያለበትን ደረጃ በመረዳት አካባቢያዊ ዘላቂነት ያለው የልማት ዕድገት ማምጣት ወቅታዊና አስፈላጊ ሥራ ሆኖ በመገኘቱ በአህጉር ደረጃ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል። ይህንን አስመልክቶ በአካባቢ ጉዳይ ላይ ያተኮረ የሚኒስትሮች ስብሰባ/ African Ministerial conference on Environment-AMCEN/ ኡጋንዳ ካምፓላ ላይ ባደረገው ዘጠነኛው ስብሰባ በአፍሪካ ደረጃ አንድ አህጉራዊ የአካባቢ መረጃ መረብ/ African Environmental Information Network/ እንዲቋቋም ውሳኔ አሣልፏል። በዚህ ውሣኔ መሠረት ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ 13 አገራት ለሙከራ ይህን ሥራ እንዲሰሩ ተመርጠዋል።

ይህን ሥራ እንዲያስተባብር ኃላፊነት የጣለበት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በአገሪቱ ያሉ የአካባቢ መረጃ አመንጪዎችንና ተጠቃሚ መ/ቤቶችን በማሰባሰብና በማስተባበር አንድ አገር አቀፍ የቴክኒክ ኮሚቴ አቋቁሟል። የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ሕዝብ ነክ መረጃዎችን ሣይንሣዊ በሆነ መንገድ የሚሰበስብ፣ የሚተነትንና በሪፖርት መልክ እያዘጋጀ የሚያሠራጭ በመሆኑና የአካባቢ ጥበቃ /Environmental protection/ ጉዳይ ከሕዝብ ተነጥሎ የማይታይ በመሆኑ የአገር አቀፉ ኮሚቴ መሥራች አባል እንዲሆን ተደርጓል። ይህ ኮሚቴ የተቋቋመው በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የሚገኘውን የአካባቢ ነክ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና ፍሰት ሁኔታን የዳሰሰ ጥናት በጋራ በማካሔድና ከጥናቱ በመነሣት ደካማና ጠንካራ ጎኖችን መሠረት ያደረገ የአምስት ዓመት ሥልታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ ነው።

ጽ/ቤቱ በዚህ አገር አቀፍ ቴክኒክ ኮሚቴ ላይ የሕዝብ ጉዳይ ስታቲስቲክስ ጥናትና ምርምር መምሪያ ኃላፊን በቋሚነት እንዲሣተፉና አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርጉ ወክሏቸዋል። በዚህም መሠረት የመምሪያ ኃላፊው አገር አቀፍ ኮሚቴው

በየሣምንቱ፣ ባደረጋቸው ተከታታይ ስብሰባዎች ላይ ሙሉ በሙሉ በመሣተፍ የባለሥልጣኑ መ/ቤት የጣለባቸውን ኃላፊነት ሲወጡ ቆይተዋል። በዚህ ረገድ በኮሚቴው አባላት አስተባባሪነት አባል መ/ቤቶቹ በህግ የተጣለባቸውን ተግባርና ኃላፊነት፣ የመረጃ አዘገጃጀትና አሠረጫጨት፣ በሥራው ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል ብቃትና የመሣሪያ አቅርቦት፣ ወደፊት አገር አቀፍ የመረጃ መረቡን/Ethiopian Enviromental Information Network/ ተግባራዊ ለማድረግ ለእያንዳንዱ የኮሚቴ አባል መ/ቤት መሟላት ያለባቸውን ጉዳዮች...ወዘተ ለመረዳት የሚያስችል ሰፊ መጠይቅ በመሙላት ለአገር አቀፉ የቴክኒክ ኮሚቴ በማቅረብ ለዓላማው መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽዎ አበርክተዋል። ይህን መጠይቅ መሠረት በማድረግ የጽ/ቤቱን ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም የሚያከናውናቸውን ተግባራት ያካተተ የትንተና ሪፖርት በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቶ ለዚሁ አገር አቀፍ ኮሚቴ ቀርቧል። በአባል መ/ቤቶች የተዘጋጁትን የእነዚህን የዳሰሣ ሪፖርቶች/ Assessment Reports/ በማቀናበር አንድ ወጥ ለማድረግና ከዚህም በመነሣት አንድ አገራዊ የአካባቢ የመረጃ መረብ /Ethiopian Environmental Information Network/ ለማቋቋም የሚያስችል ሥልታዊ ዕቅድ/ Strategic Plan/ ለማዘጋጀት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የመረጃ ማዕከል ከሰኔ 24-30/1996 በናዝሬት ከተማ አንድ ስብሰባ በማካሄድ የዶክመንቶቹን የመጀመሪያ ረቂቅ አዘጋጅቶ ተመልሷል።

ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ትንበያ በፆታ፣ በክልል፣ በገጠርና በከተማ ( በሺህ)ሰኔ 24/1996 ( July 1,2004)

| ክልል | ከተማ | | | ገጠር | | | ጠቅላላ ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ትግራይ | 368 | 378 | 746 | 1,657 | 1,710 | 3,367 | 2,025 | 2,088 | 4,113 |
| አፋር | 65 | 52 | 117 | 676 | 537 | 1,213 | 741 | 589 | 1,330 |
| አማራ | 1,003 | 1,002 | 2,005 | 8,067 | 8,071 | 16,138 | 9,070 | 9,073 | 18,143 |
| ኦሮሚያ | 1,601 | 1,606 | 3,207 | 10,923 | 10,968 | 21,891 | 12,524 | 12,574 | 25,098 |
| ሶማሌ | 361 | 310 | 671 | 1,851 | 1,587 | 3,438 | 2,212 | 1,897 | 4,109 |
| ቤንሻንጉል-ጉሙዝ | 28 | 28 | 56 | 271 | 267 | 538 | 299 | 295 | 594 |
| የደቡብ ብሔር/ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች | 578 | 585 | 1,163 | 6,423 | 6499 | 12,922 | 7,001 | 7,084 | 14,085 |
| ጋምቤላ | 22 | 21 | 43 | 97 | 94 | 191 | 119 | 115 | 234 |
| ሐረሪ | 58 | 56 | 114 | 36 | 35 | 71 | 94 | 91 | 185 |
| አዲስ አበባ | 1,348 | 1,457 | 2,805 | 0 | 0 | 0 | 1,348 | 1,457 | 2,805 |
| ድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር | 136 | 136 | 272 | 49 | 49 | 98 | 185 | 185 | 357 |
| ድምር | 5,568 | 5,631 | 11,199 | 30,050 | 29,817 | 59,867 | 35,618 | 35,448 | 71,053 |

በየሣምንቱ ባደረጋቸው ተከታታይ ስብሰባዎች ላይ ሙሉ በሙሉ በመሣተፍ የባለሥልጣኑ መ/ቤት የጣለባቸውን ኃላፊነት ሲወጡ ቆይተዋል። በዚህ ረገድ በኮሚቴው አባላት አስተባባሪነት አባል መ/ቤቶቹ በህግ የተጣለባቸውን ተግባርና ኃላፊነት፣ የመረጃ አዘገጃጀትና አሠረጫጨት፣ በሥራው ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል ብቃትና የመሣሪያ አቅርቦት፣ ወደፊት አገር አቀፍ የመረጃ መረቡን/Ethiopian Enviromental Information Network/ ተግባራዊ ለማድረግ ለእያንዳንዱ የኮሚቴ አባል መ/ቤት መሟላት ያለባቸውን ጉዳዮች…ወዘተ ለመረዳት የሚያስችል ሰፊ መጠይቅ በመሙላት ለአገር አቀፉ የቴክኒክ ኮሚቴ በማቅረብ ለዓላማው መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽዎ አበርክተዋል። ይህን መጠይቅ መሠረት በማድረግ የጽ/ቤቱን ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም የሚያከናውናቸውን ተግባራት ያካተተ የትንተና ሪፖርት በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቶ ለዚሁ አገር አቀፍ ኮሚቴ ቀርቧል። በአባል መ/ቤቶች የተዘጋጁትን የእነዚህን የዳሰሣ ሪፖርቶች/ Assessment Reports/ በማቀናበር አንድ ወጥ ለማድረግና ከዚህም በመነሣት አንድ አገራዊ የአካባቢ የመረጃ መረብ /Ethiopian Environmental Information Network/ ለማቋቋም የሚያስችል ሥልታዊ ዕቅድ/ Strategic Plan/ ለማዘጋጀት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የመረጃ ማዕከል ከሰኔ 24-30/1996 በናዝሬት ከተማ አንድ ስብሰባ በማካሄድ የዶክመንቶቹን የመጀመሪያ ረቂቅ አዘጋጅቶ ተመልሷል።

ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ትንበያ በፆታ፣ በክልል፣ በገጠርና በከተማ ( በሺህ)ሰኔ 24/1996 ( July 1,2004)

| ክልል | ከተማ | | | ገጠር | | | ጠቅላላ ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ትግራይ | 368 | 378 | 746 | 1,657 | 1,710 | 3,367 | 2,025 | 2,088 | 4,113 |
| አፋር | 65 | 52 | 117 | 676 | 537 | 1,213 | 741 | 589 | 1,330 |
| አማራ | 1,003 | 1,002 | 2,005 | 8,067 | 8,071 | 16,138 | 9,070 | 9,073 | 18,143 |
| ኦሮሚያ | 1,601 | 1,606 | 3,207 | 10,923 | 10,968 | 21,891 | 12,524 | 12,574 | 25,098 |
| ሶማሌ | 361 | 310 | 671 | 1,851 | 1,587 | 3,438 | 2,212 | 1,897 | 4,109 |
| ቤንሻንጉል-ጉሙዝ | 28 | 28 | 56 | 271 | 267 | 538 | 299 | 295 | 594 |
| የደቡብ ብሔር/ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች | 578 | 585 | 1,163 | 6,423 | 6499 | 12,922 | 7,001 | 7,084 | 14,085 |
| ጋምቤላ | 22 | 21 | 43 | 97 | 94 | 191 | 119 | 115 | 234 |
| ሐረሪ | 58 | 56 | 114 | 36 | 35 | 71 | 94 | 91 | 185 |
| አዲስ አበባ | 1,348 | 1,457 | 2,805 | 0 | 0 | 0 | 1,348 | 1,457 | 2,805 |
| ድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር | 136 | 136 | 272 | 49 | 49 | 98 | 185 | 185 | 357 |
| ድምር | 5,568 | 5,631 | 11,199 | 30,050 | 29,817 | 59,867 | 35,618 | 35,448 | 71,053 |

# ዓቢይ ሐሳብ

## የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ እንቅስቃሴ አጭር መግለጫ

ገበየሁ አበልቲ

የቴክኒክ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ

የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በ1999 የሚያካሂደውን አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለማከናወን ካቀዳቸው አበይት ዝግጅቶች መካከል ዋነኛው የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ነው። የዚህ ተግባር ዋነኛ ዓላማ በቆጠራ ወቅት አንድ ሰውና አንድ ቤት ሳይቆጠር እንዳይቀርና ተደግሞ እንዳይቆጠር፣ ለማድረግና ሌሎችንም ጠቃሚ መረጃዎች ለማስገኘት ነው። ስለሆነም ጽ/ቤቱ ይህን ግዙፍ ተግባር ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

ጽ/ቤቱ ቀደም ሲል በ1995 ዓ.ም ተጀምሮ በበጀት እጥረት ምክንያት ተቋርጦ የነበረውን የቆጠራ ሥራ ለማስጀመር ተፈቅዶ በነበረው በጀት ለካርታ ሥራው የሚያስፈልጉ የተለያዩ ቅፆችንና ካርታዎችን በማተም ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደረገ ሲሆን ከተባበሩት መንግሥታት ሥነ ሕዝብ ፈንድ UNFPA በእርዳታ ለተገኙ ተሽከርካሪዎች አስፈላጊው የጉምሩክ የአሠራር ሒደትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በአስቸኳይ እንዲጠናቀቁ ተደርጎ ለመሥክ ሥራ እንዲሰማሩ ሆኗል።

በዚህም የቆጠራ ካርታ ሥራው ከነሐሴ 18/1995 ጀምሮ በ45 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ቡድኖች በሦስት ክልሎች ማለትም በአማራ፣በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በመሰራት ላይ ይገኛል።

ሥራውን በሚመለከት በዕቅድ የተያዘው እያንዳንዱ ቡድን በወር 30 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ይሠራል በሚል ተገምቶ የነበረ ሲሆን በጽ/ቤቱና በካርታ ሠራተኞች የሥራ ትጋት እስከ ሰኔ 30/1996 ድረስ 17,926 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ተጠናቋል። በዕቅዱ መሠረት ይዘጋጃል ተብሎ የተገመተው 14,850 (45x11x30) የቆጠራ ቦታ ካርታ ሲሆን የተሠራው ከሚጠበቀው በ 3076 ወይም 20.7% ብልጫ አሳይቷል። ይህ የመላውን ሠራተኛ ጥረት የሚያመላክት መልካም ርምጃ ነበር።

ባጠናቀቅነው የበጀት ዓመት በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ከሲራሮ ወረዳ በስተቀር፣ በሰሜን ሸዋ፣ በምዕራብ ሸዋና በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው የተጠናቀቀ ሲሆን በአርሲ ዞንም በመገባደድ ላይ ይገኛል። በተመሳሳይ ሁኔታ በአማራ ክልል፣ በሰሜን ሸዋ ዞንና በደቡብ ብሄር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል በጉራጌ፣ በከምባታ ጥምባሮ፣ በሐዲያ፣ በስልጤና አላባ ዞኖች የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው ተጠናቋል። በወላይታ፣ በሲዳማና በጌዴኦ ዞኖች ይኸው ተግባር እየተካሄደ ይገኛል።

በመካሄድ ላይ የሚገኘው የቆጠራ ካርታ ሥራ የቴክኒክ አሠራር መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ በሥራው ላይ የተሠማሩ ሠራተኞችም የሥራን ዲሲፕሊን ተከትለው የተጣለባቸውን ኃላፊነት እየተወጡ ስለመሆናቸውና ሌሎች ተዛማጅ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለመከታተል በተለያዩ ጊዜያት የጽ/ቤቱ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የመስክ የሥራ ግምገማ ያደርጋሉ። ግምገማው የመማማሪያ የልምድ መለዋወጫና ለተፈጠሩ የአሠራር ስህቶተች የማረሚያ መድረክ እንዲፈጥር ታስቦ የሚዘጋጅ ነው።

የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በ1999 ዓ.ም የሚያካሒደውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባር በውጤት ለመቋጨት እንዲቻለው መላው ሕዝብ የመረጃን ጠቀሜታ በመረዳት ከቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው ጀምሮ መረጃ በመስጠትና የካርታ ሠራተኞችን መንገድ በመምራት ትብብሩን መግለጽ ይኖርበታል። ይህ መረጃ አስፈላጊነቱና ጠቀሜታው ለተወሰነ ክፍል ብቻ አለመሆኑን በመረዳት የተለመደ ድጋፍና ተሳትፎ ወሳኝ ነው።

ትክክለኛ ጠቀሜታው ለአንድ የተወሰነ ክፍል ብቻ ሳይሆን ይልቁንም የእያንዳንዱን የመረጃ ፈላጊ ጥያቄ የሚመልስ ስለሆነ ይህ አገር አቀፋዊ ግዙፍ ተግባር ግቡን ይመታ ዘንድ የፌዴራሉን መንግሥት፣ የክልላዊ መንግሥታትን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና በአጠቃላይ የቆጠራ ቦታ ካርታው እየተሰራ ያለባቸውን ወረዳዎችና ቀበሌዎች ነዋሪዎች መልካም ትብብር በእጅጉ ይጠይቃል።

# ወቅታዊ ዓምድ

## ስትራተጂክ ዕቅድ ( 1997 — 1999)

ሀገራችንን ካለችበት የድህነትና የኋላቀርነት ሁኔታ በማላቀቅ ሕብረተሰቡን ወደ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ለማድረስ ፈጣን ልማትን መሰረት ያደረጉና የተሻለ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገትን ለማምጣት የሚያግዙ ፖሊሲዎች ተነድፈውና ስትራተጂዎች ተቀርፀው ሥራ ላይ መዋል ይኖርባቸዋል። በአሁኑ ወቅት እነዚህን...ዕቅዶች በተግባር ለመተርጎም ደግሞ ልዩ ልዩ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ተግባራዊ መሆን አለባቸው። እነዚህን ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች፣ ለመንደፍም ሆነ የሚወጡ ዕቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግና ውጤታማነታቸውን ለመገምገም ወቅታዊ የሥነ-ሕዝብ መረጃዎች አስፈላጊ ናቸው።

በየትኛውም የሴክተር መ/ቤት መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በዕቅድ ላይ የተመሠረተ፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መርሁ ያደረገ አመራር ያስፈልጋል። ይህን መሰል ሥርዓት ለመዘርጋትም ውጤታማ የዕቅድ አወጣጥና የአፈፃፀም መለኪያ ስልት መቀየስ አማራጭ የማይገኝለት የእድገት ጎዳና ነው።

በመሆኑም የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ከተሰጠው ተልዕኮ አንፃር የረጅም ጊዜ ራዕይ ቀይሶ፣ ራዕዩን እውን ለማድረግ ካለበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘበና ሊተገበር የሚችል የረጅም እና የአጭር ጊዜ ዓላማና ግቦችን ያመላከተ የሦስት ዓመት (ከ1997-1999) ስልታዊ ዕቅድ በመንደፍ በእቅዱ መሰረት ወደ ታለመው ግብ ለመድረስ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል።

ጽ/ቤቱ በራዕይነት የቀየሰው «የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል መሠረት የሚሆን ሕዝብና ቤትን የተመለከተ ወቅታዊና አስተማማኝ መረጃ ያላት ኢትዮጵያን ማየት» ሲሆን ራዕዩን እውን ለማድረግም የሚከተለውን የረጅም ጊዜ ዓላማ (goal) እና የአጭር ጊዜ ስትራተጂክ ዕቅድ ግቦች ( Objectives) ነድፏል።

*ዓላማው፡- በአገሪቱ የሕዝብና ቤት መረጃ አሰባሰብ፣ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል ሲሆን የስትራተጂክ ዕቅድ ግቦቹም፡-*

- *የሁለተኛውን ዙር የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት / DHS/ በመጋቢት ወር 1997 ዓ.ም ማካሄድ፣*
- *በ1998 የካቲት ወር ላይ ሳይንሳዊ የአሠራር ደረጃውን የጠበቀ የሙከራ ቆጠራ በማካሄድ በቀጣይ 3 ወራት ውስጥ የግምገማ ሪፖርት በማጠናቀቅ በአፈፃፀም ሂደት መጠቀም፣*
- *የቆጠራ ቦታ፡- የመቆጣጠሪያ እና የወረዳ ካርታ የመስክ ሥራውን በማጠናቀቅ ለቆጠራው አደራጅቶ ዝግጁ ማድረግ፡-*
- *እስከ የካቲት 1999 ዓ.ም መጀመሪያ ድረስ የቆጠራ ቦታ የቀበሌና የወረዳ እንዲሁም የከተሞች ካርታ ዲጂታይዝ የማድረግና የማተም ሥራ ማጠናቀቅ፣*
- *የካቲት 1 ቀን 1999 ዓ.ም ሦስተኛውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ በመላ አገሪቱ ማካሄድ፣*
- *አግባባዊ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ምዝገባ አሠራርን በሁሉም ክልሎች በዕቅዱ ዘመን ማስጀመር፣*
- *የድህረ ቆጠራ ጥናት ( PES) አካሂዶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ/ Preliminary/ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለመንግስት ማቅረብ ናቸው።*

"አንድ አይነድ አንድ አይፈርድ " እንዲሉ ጽ/ቤቱ የረጅም ጊዜ ራዕዩንም ሆነ የማስፈፀሚያ ዓላማውንና ግቦቹን ለማሳካት በመደጋገፍና በቅንጅት በግምባር ቀደምነት አብረውት የሚሰሩ አቻ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ለይቷል። እነዚህ ተቋማት ባለድርሻዎች ( Stakeholders) እና የሥራ ተባባሪዎች (Collaborators) በመባል በሁለት ይከፈላሉ። ባለድርሻዎች የሚባሉት ከጽ/ቤቱ አጠቃላይ የሥራ ባህርይ አንፃር በእንቅስቃሴው ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ወይም

የጽ/ቤቱ ሥራ ተፅዕኖ ሊያሳድርባቸው የሚችል አካላት እንዲሁም በጽ/ቤቱ ሥራ ላይ ፍላጎትና የመጠየቅ መብት ሊኖራቸው የሚችሉ ተቋማት ናቸው። በሌላ አነጋገር በሥራ ሒደት ከጽ/ቤቱ ጋር ተመጋጋቢ የሆኑ ተቋማት ማለትም የእነሱ አስተዋፆ ለጽ/ቤቱ ሥራ ስኬት የግድ የሚያስፈልግ የጽ/ቤቱም አስተዋፆ የሚያስፈልጋቸው ተቋማት ናቸው።

የጽ/ቤቱ የሥራ ተባባሪዎች የሚባሉት ደግሞ የጽ/ቤቱ የተሻለ የሥራ ውጤት እንዲኖረው በአጋርነት አብረውት ሊሰሩ የሚችሉ ተቋማት ሲሆኑ ከነዚህም መካከል የማስታወቂያ ሚኒስቴርን ለአብነት ብንወስድ ሚኒስቴሩና ጽ/ቤቱ ለልማት ጠቃሚ በሆኑ የሥነ-ሕዝብ መረጃ ፍሰት ላይ በጋራ በመስራት ለህዝቡ ተገቢውን መረጃ በመስጠት ህዝብና ልማት ያላቸውን ቁርኝት በተመለከተ የህብረተሰቡን አመለካከት ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ እንዲል ማድረግ ይቻላቸዋል።

ለስትራተጂክ ዕቅዱ ስኬት የጽ/ቤቱ ውስጣዊ ጥንካሬና ድክመት እንዲሁም ውጫዊ መልካም አጋጣሚዎች (opportunities) እና ስጋቶች (Threats) ከነትንታኔአቸው በዕቅድ ሰነዱ ውስጥ ተካተዋል። ጠንካራና ደካማ ጎኖች በጽ/ቤቱ የሥራ ሂደት እና የአፈፃፀም ብቃት ላይ ተፅዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ክስተቶች እንደመሆናቸው መጠን እነዚህን ሁኔታዎች ለይቶ ማወቅ ደካማ ጎኖቹ የሚሻሻሉበትን እንደዚሁም ጠንካራ ጎኖቹ የበለጠ የሚጎለብቱበትን መንገድ ቀይሶ ለመንቀሳቀስ ያስችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች መነሻቸው ከጽ/ቤቱ ቁጥጥር ውጪ በሆኑ ሁኔታዎች አማካኝነት እንደመሆናቸው በጽ/ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ የሚያሣድሩትን ተፅዕኖ በመለየት አስፈላጊውን ዝግጅት በወቅቱ ለማድረግ እንዲቻል ትንተናው ተደርጓል።

# ሥነ ሕዝብና ኤድስ

## የዓለም ሕዝብ እድገት

በዘመናችን ኤች አይ ቪ ኤድስ እያስከተለ ካለው ከፍተኛ የሞት መጠን የተነሳና የወሊድ ቁጥጥር ስርጭትን መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት የዓለም ሕዝብ እድገት እንደሚቀንስ ቢጠበቅም የተባበሩት መንግሥታት እ.ኤ.አ በ2002 ባወጣው ትንበያ መሠረት አሁንም እጅግ ድሃ በሆኑ ሀገሮች የህዝቡ ቁጥር እጅግ እያሻቀበ እንደሚገኝ ያመላክታል።

በዚሁ ትንበያ መሠረት አሁን ያለው 6.3 ቢሊዬን የዓለም ሕዝብ በ2050 ወደ 8.9 ቢሊዬን እንደሚደርስ የተገመተ ሲሆን ከዚሁ አህዝ ውስጥ 2.6 ቢሊዬን ጭማሪ በማደግ ላይ ባሉ የአፍሪካ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሐገራት እንደሚሆን ተገምቷል። በዚህም በትንበያው መሠረት የ49 እጅግ ኋላቀር ሐገራት ሕዝብ ብዛት አሁን ካለው 668 ሚሊዬን በማሻቀብ በ2050 ወደ 1.7 ቢሊዬን ይደርሳል ተብሎ ተገምቷል።

የመንግሥታቱ ድርጅት ሥነ ሕዝብ ድርጅት በትንበያው በ2050 በኤድስና ተዛማጅ በሽታዎች 278 ሚሊዬን ሕዝብ ለሕልፈተ ሕይወት እንደሚዳረግም አመልክቷል።

ምንጭ፣ ስቴት ኦቭ ዎርልድ ፖፑሌሽን 2003

## ታይላንድና የፀረ-ኤድስ ዘመቻዋ

ታይላንድ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን በመቆጣጠር ታላቅ ውጤት ካስመዘገቡ አገሮች አንዷ ስትሆን ሐገሪቱ የበሽታውን ስርጭት ለመግታት በዋናነት የተጠቀመችው ኮንዶም በማሰራጨት እንደሆነም የሀገሪቱን የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ የገለፀው መረጃ ያመላክታል።

ባሁኑ ወቅት የሀገሪቱ የኮንዶም ስርጭት ወደ 100 ፐርሰንት ያደገ ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኤድስ ፕሮግራም ጽ/ቤት በቅርቡ ባወጣው መረጃ መሠረት እ.ኤ.አ በ1991 በየዓመቱ 140ሺ ሰዎች በቫይረሱ ይያዙ እንደነበርና ሐገሪቱ ባደረገችው ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫና የኮንዶም ስርጭት ዘመቻ ከላይ የተጠቀሰው ቁጥር በ21 ሺ ያህል ለመቀነስ እንደቻለ ተመዝግቧል።

ከዚህም በላይ ሀገሪቱ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ክትባት ዘመቻንም አጠናክራ መቀጠሏንና አሁን ክትባቱን በሰው ላይ ለመሞከር በዝግጅት ላይ መሆኗም ታውቋል። የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መድኃኒቶችን ማምረት የጀመረችው ታይላንድ በ2000 ዓ.ም ለ2095 ሰው ብቻ ይዳረስ የነበረው መድሀኒት እስካለፈው ሚያዚያ ወር ድረስ 27ሺ ሰዎች መድኃኒቱን ለማግኘት ችለዋል። በሐገሪቱ የኤድስ ዓለም አቀፍ ጉባኤ በተከፈተበት ዕለት የታይላንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳስታወቁት ሀገሪቱ ወደፊት የእድሜ ማራዘሚያ መድኃኒቱን ያለ ክፍያ በነፃ ለማቅረብ እንደተዘጋጀች የገለፁ ሲሆን ለግሎባል ፈንድም በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት የገንዘብ ዕርዳታ ለመስጠት ቃል ገብተዋል።

ምንጭ አዲስ ልሳን ሐምሌ 21/96

## ኤድስና ሠራተኛው -ዓለም አቀፋዊ ስጋት

በሐገረ-ዝምባቤ የሚታተመው «ዘ ሔራልድ ሐራሬ» የተባለው ጋዜጣ ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ድርጅትን (ILO)ጠቅሶ በደህረ ገጽ ባስተላለፈው መረጃ ኤድስ በቀጣዮቹ ዓመታት የሚያስከትለውን አደጋ እንደሚከተለው አስፍሯል።

- በአሁኑ ወቅት 3.65 ሚሊዩን ሠራተኛ በኤድስ ቫይረስ እንደተያዘ ተገመቷል።
- 2005 የፈረንጆች ዓመት 28 ሚሊየን ለሕልፈተ ሕይወት ይዳረጋል። ከዚሁ ሚች ቁጥር አብዛኛው አፍሪካዊ ሠራተኛ ይሆናል። በዚሁ ዓመት 2 ሚሊዩን ሠራተኛ ከሕመሙ የተነሣ መሥራት ይሳነዋል።
- በ2010 ከህክምና እጦት የተነሣ 48 ሚሊዩን ሠራተኛ በኤድስ ይሞታል። ብዙ የሥራ መደቦችም ክፍት ስለሚሆኑ በጤነኛ ሠራተኞች ላይ የሥራ ጫና ይፈጠራል።

## ለግንዛቤዎ!

**የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ምንነትና ፋይዳ/Significance/**

(ጥላዬ ገረሱ)

ሕቤቆኮ ጽ/ቤት

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሕዝብ የክብር መዝገብ አሠራርን አስመልክቶ በወጡ ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ ጽሑፎች እንደተገለፀው ዋነኛ <u>ወሳኝ ኩነቶች</u> ተብለው የሚታወቁት ልደት፣ የሽል ሞት፣ ሞትና ጋብቻ፣ ፍቺ ናቸው። ወሳኝ ኩነት የተባሉበት ዋና ምክንያት የአንድን ሀገር ሕዝብ ብዛት ስለሚወስኑ፣ ለሕብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ግልጋሎት ለሚነደፉ ዕቅዶች ዝግጅት፣ ክትትልና የአፈጻጸም ግምገማ ለማድረግ ወሳኝ የመረጃ ምንጮች በመሆናቸውና በየሐገሮቹ የተደነገጉ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለመጠበቅ መነሻ የሚሆኑ ወሳኝ የሆኑ ግላዊ መረጃዎች በመሆናቸው ነው።

እነዚህ ግላዊ መረጃዎች በሕግ በተቋቋሙ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና በስታቲስቲክስ ሥርአቶች አማካይነት ይገኛሉ። ከምዝገባው አላባዊያን /Elements/ መካከል ለምሳሌ ልደትና ሞትን ብንወስድ እነዚህ ኩነቶች የሕዝብን ብዛት ዕድገት ምጣኔ በዋነኛነት በቀጥታ ይወስናሉ። ምክንያቱም የሕዝቡ ቁጥር እየጨመረ፣ እየቀነሰ ወይም ባለበት ሊቆይ የሚችለው በዋነኝነት በየዓመቱ በሚከናወን ልደትና ሞት መካከል ባለው ልዩነት መጠን ነው። በየዓመቱ የሚወለደው ቁጥር ከሚሞተው የበለጠ፣ ያነሰ ወይም እኩል ከሆነ የሕዝቡም ብዛት በዚያው መሠረት እየጨመረ፣ እየቀነሰ ወይም ባለበት ይቆያል።

ከዚህም በላይ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አስተዳደራዊና ሕጋዊ ስታቲስቲካዊ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል። ከአስተዳደር አንጻር፦ በሕብረተሰቡ ውስጥ በየዓመቱ የሚወለዱትን ሕጻናት፣ የሟቹን ቁጥር፣ የጋብቻና ፍቺን ብዛት ማወቅ የእናቶችንና የሕፃናትን ጤንነት ለመጠበቅ አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ፣ የአስተማሪዎችንና የትምህርት ቤቶችን ብዛት ለመተንበይና ብሎም መምህራንን ለማሠልጠንና ት/ቤቶችን ለመሥራት፣ የጤና ባለሙያዎችንና ተቋማትን ለማዘጋጀት እና የመሳሰሉትን ማህበራዊ ፍላጎቶች በእቅድ ለመምራት ይጠቅማል።

በሕግ በኩል ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት የሰዎች የልደት ጊዜ፣ ከማን እንደተወለዱ፣ የት እንደተወለዱና የጋብቻ ሁኔታዎችን...ወዘተ የሚያመለክት መረጃ ለትምህርት፣ ለጋብቻ፣ ለውርስ፣ ለኢንሹራንስ፣ ለመምረጥ ወይም ለመመረጥ፣ ለጡረታና እንዲሁም ለውትድርና አገልግሎት ለመመልመል በመረጃነት ያገለግላል። ይህን ጠቀሜታ ዘርዘር አድርገን ስንመለከተው ለምሳሌ የሞት ምዝገባን ብንወስድ የአንድ ሰው መሞት በሕጋዊ መንገድ ከታወቀ ተመዝግቦ የሚያስገኘው ሕጋዊ የምስክር ወረቀት የሟች ዘመዶች ውርስ፣ ኢንሹራንስ፣ ጡረታ ...ወዘተ እንዲያገኙ በመረጃነት ይጠቅማል። በተመሳሳይ መልኩ ሕጋዊ ጋብቻ በወቅቱ ከተመዘገበ ለተጋቢዎች የምስክር ወረቀት የሚያስገኝ ሲሆን ይህ የምስክር ወረቀት በጋብቻ ላይ ለሚነሱ ክርክሮች እንደ ማስረጃ ያገለግላል። በተጨማሪም ከሁለቱ ተጋቢዎች የሚወለዱ ልጆች የወላጆችን እንክብካቤ የማግኘት መብታቸው እንዲጠበቅ ከማድረጉም በላይ ለውርስ፣ ለኢንሹራንስ...ወዘተ መብቶች ማስከበሪያ ሕጋዊ መረጃ ይሆናል።

ስታቲስቲካዊ ፋይዳውን ስንመለከት ደግሞ ስታቲስቲክስ የሕብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ፣ የሥነ-ሕዝብ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱ አሀዛዊ መረጃዎችን በሳይንሳዊ መንገድ ሰብስቦ፣ ተንትኖና አጠናቅሮ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እቅድ ዝግጅት ስለሚያስራጭ ይህን መረጃ መሠረት በማድረግ በየዓመቱ ስንት ልጅ እንደተወለደ፣ ስንት ሰው እንደሞተና ስንት ጋብቻዎች እንደተፈፀሙ የሚያሣውቅ መረጃ ለማግኘት ያስችላል። መረጃውም የአሁኑንና የወደፊቱን የሕዝብ ብዛት ዕድገት ለማወቅ ወሳኝ ስለሆነ ማናቸውንም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕቅዶች ዓላማ በማሳካት የሕብረተሰቡን እድገት ለማሻሻል የየዓመቱን የሥነ-ሕዝብ በተለይም የወሳኝ ኩነቶችን መረጃ ማግኘት እጅግ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ኢትዮጵያ ከላይ በተጠቀሱት ፋይዳዎች ተጠቃሚ እንድትሆን በሐገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሰርዓት ለማቋቋም በስድስት አርዕስቶች ላይ ቴክኒካዊ ጥናቶችን አዘጋጅቷል። በሥርዓቶቹ ውሰጥ ሁለት ዋና ዋና ተግባራት የሚከነወኑ ሲሆን እነሱም፦

*ሀ) የወሳኝ ኩነት ምዝገባና*

*ለ) የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ ናቸው።*

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ማለት ተከታታይ፣ ቋሚና አስገዳጅ የሆነ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍች ኩነቶችንና ከኩነቶቹ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ የሥነ-ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህሪያትን ጭምር መመዝገብ ማለት ነው።

የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ፣ ማለት ደግሞ አጠቃላይ የወሳኝ ኩነቶችን ብዛት፣ የኩነቶችንና ከኩነቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ-ሕዝብና ማህበራዊ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱ አሀዛዊ መረጃዎችን በሳይንሳዊ መንገድ መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማጠናቀርና ውጤቱን ለኢኮኖሚያዊና ለማህበራዊ ዕቅድ አዘጋጆች፣ ለተመራማሪዎችና ለሌሎች መረጃ ተጠቃሚዎች የማሰራጨት ተግባር ነው።

በዚህም መሠረት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በሕገ መንግሥቱና በማቋቋሚያ አዋጁ መሠረት ከተቀመጡለት ሁለት ዓላማዎች አንዱ የሆነውን የሕዝብና ቤቶች ምዝገባ በመላ ሀገሪቱ እንዲቋቋምና እንዲሠራበት በየአስተዳደር እርከኑ አስፈፃሚ ተቋማት እንዲደራጁ መንገድ ለመቀየስ እንዲቻል በጽ/ቤቱ የቴክኒክ መመሪያዎችና የድርጊት መርሃ ግብሮች ይዘጋጃሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ፒራሚድ: 1996




የከተማው ሕዝብ ፒራሚድ: 1996




የገጠሩ ሕዝብ ፒራሚድ: 1996



# የግጥም ጫፍ

## እያለን የለንም

የርምጃችን ርቀቱ - ባቅማችን ካልተወሰነ፣
የመኖር ዕዳ ስንቃችን - በጊዜ ካልተከወነ፣
የወጣት ትኩስ አቅማችን - ባልባሌ ከባከነ፣
የማታ መቆያ እንጀራ - ከሥራ ካልተዘገነ፣
እየቻልን ሳንችል ከቀረን - በዘመን ስናመነታ፣
ያኔ እያለን የለንም - ከብልሆች ሠፈር ተርታ።

/ውድአላት ገዳሙ ፦ በ1996 ዓ.ም ካሳተመችው«እናትና ልጅ »መጽሐፍ የተወሰደ/

## የአዲስ ዓመት ስጦታ!

ስሥራውመሳካት ጥራችሁ ግራችሁ
የሙያውን እውቀት በትጋት ቀስማችሁ
የጊዜን ምንነት በውል ተረድታችሁ
ሌት ከቀን ሳትሉ በትጋት ሠርታችሁ
ቲዎሪውን በተግባር የተረጎማችሁ
በቴክኒክ በሙያው የሰለጠናችሁ
ብቃትን ከጥራት የተሳበሳችሁአቅዳችሁ
ሰምሮ ተሳክቶ ህልማችሁ
ካርታ ሠራተኞች እናንተ ሁላችሁ
በጽ/ቤት ሆነ በመስክም ያላችሁ
ትናንትና ዛሬ ለዚህ ከበቃችሁ
ለነገን ጠንክሩ አንኳን ደስ ያላችሁ።

ለሕቤቆኮ ጽ/ቤትና ለረዳት ካርታ ሠራተኞች
አዳነ ቸርነት
ረዳት ካርታ ሠራተኛ

## በሕይወት ሁሌም፡-

- እንደሰው ደካማ ጎንህን እወቅ፣ ለመሻሻል ሞክር እንጂ ድክመትህን በብልጠት ለመሸፈን አትሞክር
- ለማወቅና ለመማር ጥረት አድርግ፣ አላዋቂ አባላለሁ ብለህ ጠይቆ ከመረዳት አትቦዝን
- ጊዜህን በእቅድ ተጠቀም፣ ዘወትር በጊዜ የመጠቀም ልምድህን አዳብር
- የሰዎችን ማንነት ለማወቅ እንድትችል ትዕግሥት ይኑርህ፣ በትክረት ተረዳቸው እንጂ በይሆናል የፈጠነ ግምት ስለሰዎች ባህርይ ውሳኔ ላይ አትድረስ
- በጋራ የመስራት፣ በጋራ የመኖር በጋራ የመጠቀም ልምድ ይኑርህ
- ሀገርህን ውደድ፣ ሕዝብህን አክብር በሀገርና በወገን ላይ የሚሰነዘሩ ተገቢ ያልሆኑ ትችቶችን ሁሉ በመቋቋም በዝምታ አትለፍ መሰዋዕት የሚጠይቅ ቢሆንም እንኳ ወደኋላ አትበል

አዳነ ቸርነት
ረዳት ካርታ ሠራተኛ
ምንጭ ያልታወቀ

# ትዕግስት

ደረጃ ታደሰ ረዳት ካርታ ሠራተኛ

ኖኖ ወረዳ -ምዕራብ ሸዋ

ነገሩ የሆነው ሰኔ 7/96 ዓ.ም ነበር። ልዩ ስሙ « ሚጣሪ ሄበኔ »በሚባል ቀበሌ ውስጥ ነው። ጓደኛዬ ዲቪ ሉተሪ ወጥቶለት ሥራ ስለለቀቀ ብቻዬን ካርታ ሳነሳ በመዋሌ ሳላስበው ሰዓቱ 12:30 ሆኖ መሸቷል። ይታያችሁ የምገባው 2:30 የሚፈጅ «ሰልክ አምባ» የሚባል ቦታ ነው። ሥራዬን ጨርሼ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ያውም ዝናብ እየጣለ ጉዞዬን ጀመርኩ። ቀኑ ስለመሸ አቅጣጫዬን መለየት ባለመቻሌ ወደቀኝ ስሄድ ጥሻው ወደ ግራ እየመሰለኝ ወደግራ ስሄድም ወደቀኝ እየወሰደኝ በጫካው ውስጥ ጉሬዛ ከዛፍ ዛፍ ሲዘል ተናካሽ አውሬ እየመሰለኝ ልቤ በፍርሃት ሲርድ፣ አውሬውን ለማምለጥ በማሰብ ዘልዬ ጉድጓድ ውስጥ ገባሁ። ምንም እንኳን ዝናቡ እጅግ የበረታ ቢሆንም ከመብረድ ይልቅ ከሰውነቴ የሚወጣው የፍርሀት ላብ ልብሴን አርሶታል። አይ ፍርሐት! ምን ነካኝ ጃል ድሮ በኔ እድሜ ቀጭኔና ዝሆን አደን አባቶቼ ጫካ ውስጥ ያድራሉ ሲባል ሰምቼ የለም እንዴ! አሁን ራሴን አጠነከርኩት። እንደምንም ብዬ ጀገን ጀገን አልኩና ከገባሁበት ጫካ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ ለመውጣት ቻልኩ ። ወዲያው ከፊት ለፊቴ አንዲት ደሳሳ ጎጆ በማየቴ በጉጉት ተጣራሁ። ባለቤቶቹ ቤት ሆነው ምን እንደምፈልግ ጠየቁኝ። ስለመሸብኝ እንዲያሳድሩኝ በሚቀራረጥ ድምጽ ለመንኳቸው። ሆኖም በቤቱ ውስጥ የነበሩት ሴቶች ብቻ በመሆናቸው በራቸውን ለመክፈት ተጠራጠሩ። እኔም እንደማይከፍቱልኝ ሳውቅ ይበልጥ ጉልበት ጨምሬ እንደመኪና በረርኩ። ወዲያውም "ወሪቤሳ" የሚባል ወንዝ ስደርስ ነፍሴ መለስ አለች። ያለ የሌለ ኃይሌን ሰባስቤ «ሰልክ አምባ» ከምሽቱ 4:30 ላይ ደረስኩ አላችኋለሁ። ያለወትሮዬ በማምሸቴ ጓደኞቼ ሲያገኙኝ በደስታ ጮሁ። እኔም በድካም አልጋዬ ላይ ተዘርሬ የሆነውን ሁሉ ነገርኳቸው። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን አልተበገርኩም፣ ጠዋት ተነስቼ እዚያው ቀበሌ ተመልሼ የቀረውን ሥራ ለማጠናቀቅ ገሰገስኩ። ቆራጥነት ይሏችኋል ይኸው ነው።የቀጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ደግሞ ጥንካሬንና ብርታትን የሚጠይቅ ታላቅ ሀገራዊ ክንውን ነው።

በየትኛውም አቅጣጫ የምትገኙ ውድ የሥራ ባልደረቦቼ! ይህ ሥራ ትዕግስትን፣ ጥንካሬን እና ድፍረትን የሚጠይቅ ነው። ሥራችን አድካሚና እልህ አስጨራሽ በመሆኑ ለጊዜው ልንቸገር እንችላለን። ይሁን እንጂ ዛሬ እኛ በሰበሰብነው መረጃ ነገ ሀገርን ከድህነት ሕዝብን ከርሐብ ለማላቀቅ ሁነኛ አስተዋፅኦ ማበርከቱን ስናስብ ያኔ የዜግነት ኩራትና እፎይታ ይሰማናል። የዚህ ዕድል ተቋዳሽ መሆኑም በራሱ ታላቅ አጋጣሚ ነውና እንበርታ! እኛ ወጣቶች ካልበረታን ማን መጥቶ ሊሠራልን ይችላል። በሉ ወደፊት በቀጣዩዋ የዜና ቆጠራ መጽሔት እንገናኛለን።

መልካም የሥራ ዘመን

# Selected Quotations

If you put good people in bad systems you get bad results. You have to water the flowers you want to grow.

Stephen R.covey

The greatest things are accomplished by individual people, not only by committees or companies.

Alfred A. Montagert

Individual commitment to a group effort-that is what makes a team work, a company work, a society work.

Vincent Lombard

It is only as we develop others that we permanently succeed.

Anonymous

Source, internet

## የኮሚሽኑ ጽ/ቤት እሴቶች ( VALUES)

**ወቅታዊነት፥** አስተማማኝና ጥራታቸው የተጠበቀ የሥነ-ሕዝብ መረጃዎችን ተጠቃሚዎች በሚፈልጉበት ወቅት ማቅረብ፣

**ምስጥራዊነት፥** የግለሰቦችን መረጃ ምስጢራዊነት ማክበርና መጠበቅ፣ ከመረጃ ሰጪዎች የተገኙ ግለሰባዊ መረጃዎችን ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ አለመስጠት፣

**በጋራ መሥራት፥** የተገልጋዮችን የመረጃ ፍላጎት የሚያሟላና ጥራቱ የተጠበቀ፣ ወቅታዊ መረጃን ከባለድርሻዎችና ተባባሪ የመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት፣ከግለሰቦችና ከህብረተሰብ ጋር በቅንጅት መሥራት፣

**አሳታፊነት፥** የጽ/ቤቱ ሥራ አመራር በሚያከናውናቸው ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ተግባራት ግልጽነትንና በየደረጃው ያሉ ሠራተኞችን የሚያሳትፍ አመራር የመስጠት መርህን የሚከተል መሆን፣

**ታማኝነት፦** ከመንግሥትና ከለጋሽ ድርጅቶች የሚገኘውን ገንዘብና ቁሳቁስ ሃላፊነትና ተጠያቂነት ባለበት መንገድ ሥራ ላይ ማዋል፣ለሙያ ታማኝ መሆን፣

**የሥራ ተነሳሽነት፦** በባለቤትነትና በተጠያቂነት መንፈስ የሥራ ኃላፊነትን በብቃት መወጣትን መርህ ማድረግ፣

**ብቃት፦** የሥራ ባለድርሻዎችንና ተባባሪዎችን ፍላጎት ለማርካት የሙያ ብቃት ማሳደግ፣በትጋትና በከፍተኛ የሥራ ፍቅር ኃላፊነትን መወጣት፣

**ደረጃውን የጠበቀ መረጃ፦** በማናቸውም የጥናት ሥራዎች ዓለም አቀፍ የስታቲስቲክስ ሜቴዶሎጂን መጠቀም፣ ሳይንሳዊ የመረጃ አሰባሰብ፣ አጠናቃቀርና ሥርጭት አሰራርን ማስፈን፣

# እንኳን ደስ አላችሁ!

## CONGRATULATIONS!



ምኒሊክ ፀጋ ኤም.ኤስ.ሲ
በስታቲስቲክስ



ወንድወሰን ካሣሁን ኤም.ኤስ.ሲ
በስታቲስቲክስ

### *Success*

*Talent, Chance and perseverance*
*Are the right Mixes*
*Behind every success.*
*Time, manner and place*
*Are also the blue prints*
*For a success.*
*( Alemu Hailu, 2004)*